
ለዓሊሁ፡ርዕሠ
ጸብር፡ዓይነማር
ያም፡ጌታሁን
1982ዓ.ም
ተሣለ።።

የእናታችን ወለተ ጴጥሮስ ገድል ረቡዕ የሚነበብ

ንፅድ ክብርት የምትሆን ሰማዕት እና የገዳማት እናት የምትሆን የእናታችን ወለተ ጴጥሮስ ገድል እና ምስክርነት ይህ ነው ልመናዋ በረከቷ ይደርብን ለዘለዓለሙ። አሜን

እናቷ ክርስቶስ ዕበያም እንደ ሄደች በሰማች ጊዜ ታላቅ ኃዘንን አዘነች አብራት እንድትቀመጥና እንድታገለግላትም ኢላርያን እና አገልጋዮቿን ላከችላት።

፫፱. ያም ነፍሰ ገዳይ ተቀብሎ ንጉሥ እንዳዘዘው አደረገ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስን ወደ እሥር ቤት ጨመራት እሷም ሳትበላ ሳትጠጣ ሦስት ቀን ተቀመጠች፤ ነፍሰ ገዳዩ የረከሰ አረማዊ ነበርና። በምግባርም ሆነ በሃይማኖት ከሷ ጋር አይተባበርም ነበር፤ ክፉም ሆነ ደግ ከሷ ጋር በሚነጋገር ጊዜ ቋንቋውን አትሰማም ነበር። በእናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ላይ ስደትና መከራ የተደረገባት ይህች ሰዓት ምን ያክል የምታስፈራ ምን ያክል የምታስጨንቅ ናት! በዚያ ዘመን ክርስቲያኖችን ካገኛቸው መከራና ስደት ሁሉ ይከፋል እጅግም ያስጨንቃል። ከሴቶች መካከል እሷን የምትመስል ጨክናስ ይህን መከራ የምትቀበል ማን ናት? ለደካማይቱ ሴትስ ይቅርና ኃይል ሰተሰጣቸው ወንዶች እንኳን ታግሠው እንደሷ ይህን ይቀበሉ ዘንድ ባልተቻላቸውም ነበር አድሮባት ያለው የእግዚአብሔር ኃይል ያፀናታል ያስታግሳታል እንጂ። ሐዋርያው ጴጥሮስ “መከራን ተቀበላችሁ እሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል” (1ጴጥ 5÷10) እንዳለ።

፵. ቋንቋቸውን በምትሰማቸው ግብራቸውን በምታውቀው በክርስቲያኖች መካከል ከእነሱ ጋር በምግብ ከምትቀላቀላቸው ክርስቲያኖች ጋር አስቀምጠዋትስ ቢሆን ነገሩ ጭንቅ ባልሆነም ነበር ቀላል ቢሆን ነበር

እንጂ። ያም ነፍስ ገዳይ ባያት ጊዜ በራሱ ቋንቋ "አንች ምንድን ነሽ፣ ጠባይሽስ ምንድን ነው፣ የማትበይ የማትጠጭ አኳኋርሽስ እንዴት ይሆናል?" አላት በመካከላቸው የሚተረጉም አልነበረም፤ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ጆሮዋን ከፍቷልና ቋንቋውን ሰማችው መጽሐፍ ለዮሴፍ ‹‹ወደ ግብፅ በወጣ ጊዜ ምስክርን አቆመ የማያውቀዉንም ቋንቋ ሰማ" (መዝ 80÷4) እንዳለ ለሷም እንዲሁ አደረገላት።

ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስም መለሰችለት "እኔ ክርስቲያናዊት ስሆን ኦሪት አትዳሱት፣ አትብሉት ብላ የከለከለችውን አይጡንም እባቡንም የምትበላ የምትተወው ነገር የሌለህ በሃይማኖት ከእኔ ጋር የማትተባበር ከሐዲ ስትሆን አንተ ያዘጋጀኸውን ምግብ እንዴት እበላለሁ? አንተ በጠላህበት ጽዋስ እንዴት እጠጣለሁ?" አለችው፤ "ነገር ግን ጥሬውን እህልና ለማብሰያም የሚሆን አዲስ ሸክላና ውኃ ለመቅዳት የሚሆን አዲስ ቅል አምጣልኝ" አለችው። እሱም ቋንቋዋን ሰማ፤ እንዳዘዘችውም አደረገ፤ ከዚህ በኋላ ኢላርያ አበሰለችና አቀረበችላት ጥቂትም ቀመሰችለትና ተወችው፤ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ መብልን ስለተወች ኢላርያ አለቀሰች በዚህ ግብር ሁለቱ ብቻቸውን አንድ ወር ኖሩ፤

፹፩. በዚያ ወቅት ሰይጣን በዚያ አረማዊ ሰው ልብ ውስጥ አደረበት፤ በሷም ላይ ዐይኑን ጣለባት ወንዶች ሴቶችን በሚፈታተኑበት ግብር ይፈታተናት ጀመር፤ እምቢ ባለችው ጊዜም የፍጥኝ በገመድ ከቤቱ ምሰሶ ጋር አሥሮ አቆማት። እንጨት ሰበሰበ፤ እሳትም ከበታቿ ያነድና በጪስ ያስጨንቃት ዘንድ ጀመረ እሳቱም ጠፋ አልነደደም ጢሱም አልጨሰም ማንደዱ በተሣነው ጊዜ ተዋት፤ ከማሰሪያዉም ፈታት ነገር ግን መፈታተኑን አልተዋትም።

ከዕለታት በአንድ ቀንም በሰይጣናዊ አሳብ ተታለሎ ፈቃዱን ይፈጽም ዘንድ አስቦ ሔደ፤ የከበረች እና የተመረጠች እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ካለችበት ቤት በገባ ጊዜ ለጸሎት ቆማ ፊቷ እንደ ፀሐይ ሲያበራ የእግዚአብሔር መላእክም በጆሮዋ አጠገብ የተመዘዘ ሠይፍን ይዞ ከሷ ጋር ቁሞ አየ፤ ያን ጊዜ ፈርቶ ወደ ኋላው ተመለሰ። የኋሊትም ወደቀ ከዚህ ዕለት ጀምሮ ተገሠፀ። ዳግመኛም አልተፈታተናትም ያከብራት እና ይፈራት ነበር እንጂ፤ ሰይጣንም አፈረ፤ ተሸነፈ፤ ለመልክአ ክርስቶስ ያልሆነውን ግብር እንደምን አስቦ የከፋ የከረፋ ባርያ ሆኖ ሳለ ለሱ እንደሚሆንለት ተጠራጠረ ይህስ የእሱ አሳብ አይደለም የሰይጣን ነው እንጂ እሱ በትዕቢቱ አምላክ መሆንን አስቧልና፤

፹፪. እኅተ ክርስቶስም ከእሷ ከተለየች ጀምሮ በቀንና በሌሊት ብቻዋን ስለቀረች እናቷን ቅድስት ቡርክት ወለተ ጴጥሮስ ስለተለየቻት ስታዝንና ስታለቅስ ኖረች። ጡት እንዳስጣሉት ሕፃን ሆነች፤ ወደ ዓመተ ክርስቶስ ሔደች በፊቷም ቆማ ፈጽማ አለቀሰች ዓመተ ክርስቶስም "አንች ሆይ! ምን ያስለቅስሻል?" አለቻት "ከእናቴ ከቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ለይተው ብቻየን ስላስቀሩኝ አለቅሳለሁ" ብላ መለሰችላት። "አሁንም እመቤቴ ሆይ! በፊትሽ ሞገስን አግኝቸ እንደ ሆነ ይቅር እንድትይኝ አለምንሻለሁ ኀዘኔንም ተመልከች ስለ እኔም መልክአ ክርስቶስን ወደ እናቴ ይሰደኝ ዘንድ ለምኝልኝ" አለቻት፤ ያን ጊዜም ልቧ ራራላት እንዳለቻትም መልክአ ክርስቶስን ጠራችው፤ እሽ በጅ አለችው።

፹፫. እሱም ወደ ንጉሥ ገብቶ በፊቱ ቆመና "ጌታዬ ንጉሥ ሺህ ዓመት ንገሥ ዛሬ በግዛትህ የሆነውን ድንቅ ነገር ሰማሁ" አለው፤ "ንጉሡም ምን አየህ ምን ሰማህ?" አለው። "ሰው ሁሉ ከዘመዶቹ ሲለዩት ሲያሳድዱት መከራም ሲያሳዩት ያለቅሳል፤ ያዝናል፤ ይህች

ከወለተ ጴጥሮስ ጋር የነበረች ሴት ግን ከወገኖችሽ ጋር በአገርሽ ተቀመጭ ብላት ታዝናለች፤ ታለቅሳለች" አለው። ንጉሡም "አንተስ ምን እንዳደርግላት ትወዳለህ?" ብሎ መለሰለት፤ "እኔስ የንዳድ በሽታ ይገድላት ዘንድ እንዳትዘበዝበን ወደዚያ አገር እንድንልካት እወዳለሁ" አለው። ንጉሡም "በዚህ ነገር ተታለለ እንዳልኸው ይሁን" አለው፤ ወጥቶም ነገራት፤ አሰናብተንሻል ሒድ አላት፤ ይህንንም ሰምታ ወድቃ እግሩን ሳመችው፤ ፈጽማም ደስ ተሰኘች እግዚአብሔርንም አመሰገነች።

ከዚህ በኋላ የተከበረችና የተመረጠች ወለተ ጴጥሮስ ወዳለችበት አገር ደረሰች፤ ከእሷ ጋርም ተገናኝታ እጅ ነሳቻት፤ ፊቷ ቅድስትና ቡርክት እናታችን ወለተ ጴጥሮስም እያረጋጋቻት "ምን ያስለቅስሻል ዛሬ እኔን ባገኘሽ ጊዜ የምትፈልጊኝ እኔን አይደለምን? ከእንግዲህስ አንቺንም እኔንም ተበትነን እንዳንቀር ይልቁንም በአንድነት አንድ ሁነን እንድንኖር ያደረገን እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባናል፤" ይህን ብላ ለቅሶዋን አስተወቻት። ከዚህ በኋላ እኅተ ክርስቶስ እና ኢላርያ ምግቧን በማዘጋጀት ሲያገለግሏት ኖሩ የተመረጠች ቅድስት ወለተ ጴጥሮስም ለእግዚአብሔር ስትገዛ ኖረች፤

፹፬. ከዕለታት በአንድ ቀን ተክለ ማርያም ወደ እናቷ ሔዶ ብዙ ገንዘብም ተቀበለ በአህያም ጭኖ ተመለሰ፤ በምድረ በዳም ሲሔድ ሰዓቱ መሸበት፤ በእንግድነት የሚያድርበት ሥፍራም አልነበረም፤ በዘንዶ ላይ በበቀለ ዛፍም ተጠለለ። ከአህያውም ላይ ጭነቱን አወረደ

እና አህያውንም በዘንዶው ላይ በበቀለው ዛፍ አሠረው። እሱም ተኛ፤ ዘንዶውን ግን አላየውም ነግህ በሆነ ጊዜ ዘንዶው ጮኸ፤ በተንቀሳቀሰም ጊዜ ዛፉን አናወጠው።

፹፫. ያም ረድዕ ባየው ጊዜ ፈራ ደነገጠ፤ ፈጥኖ አህያውን ፈታና ገንዘቡን ጭኖ እየሮጠ ሐደ፤ ከኋላው የሚከተለው መስሎታልና። ያ! ዘንዶ ሊከተለውስ ቢወድ ኖሮ ሌሊት ሲተኛ በዋጠው ነበር አህያውንም ባልተወው ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር የተመረጠችና የከበረች ወለተ ጴጥሮስ የጸሎቷን ኃይልን ይገልጥ ዘንድ ዘንዶው እንዲጮኽና እንዲንቀሳቀስ አደረገው። ዘንዶው ባይጮኽ ኖሮ ያ ረድዕ ባላየው ለእኛስ ማን በነገረን ነበር፤ እኛስ ይህን ተአምር እንዴት በጸፍን ነበር።

፹፬. ያም ረድዕ እያደነቀ ሐደ ከዚያ አገርም ደረሰ ኃዙንም ከአህያው አወረደ ወደ ተመረጠችና ወደ ከበረች እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ገባ ያመጣውንም ዕቃ በፊቷ አስቀመጠ፤ የእናቷንና የወንድሞቿን መልእክትም ነገራት፤ ሰላምታና እጅ መንሻ አቅርቦላት በፊቷ ቆመ፤ ወደ ላይና ወደታች ተመለከተችው፤ ሳይነግራት ገና "በምድረ በዳ ያገኘውን ድንጋጭ አውቃለችና ዛሬ የት አደርህ? ያገኘህስ ነገር ምንድን ነው?" አለችው፤ እንደማታውቅም ጠየቀችው እሱም የሆነውን ሁሉ ነገራት፤ እሷም ለምን "ፈራህ? ለምንስ ደነገጥህ? እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ያለ አይደለምን? መጽሐፉስ ‹እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ የሚቃወመን የለም› ዳግመኛም ‹ጸድቅ እንደ ጋሻ ይከበልል ከሌሊቱ ግርማ የተነሣም አትፈራም በተኩላዎችና በዘንዶዎች ላይም ትጫናለህ› ያለ አይደለምን (ሮሜ 8÷27፣ መዝ 90÷15) ስለዚህ የሚኾህ ሳይኖር ለምን ትፈራለህ?" አለችው።

ከዚህ በኋላ ያንን ገንዘብ ልብሱንም ወርቁንም ተቀበለችው ለዚያ ነፍሰ ገዳይ አረማዊ ሰጠችው። ከዚህ በኋላም በየቀኑ ትሰጠዋለች።

፰፮. የደግነቷን ሥራ የአጋዋንም ብዛት፣ የተሰጣትንም ሞገስ በየጊዜው ፈጽሞ ወደዳት፤ አከበራት፤ በአገሩ ቋንቋም "ስቲ" አላት፤ ሲተረጉሙትም "እመቤት" ማለት ነው። እግዚአብሔር ከከበረችና ከተመረጠች እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ጋር ነበረና። አሪት ዮሴፍን ወደ ወኅኒ ጣሉት፤ የእግዚአብሔር ረድኤት ግን ከዮሴፍ ጋር ነበር፤ ምሕረቱንና ፍቅሩን በላዩ ላይ አፈሰሰ፤ ሞገስንም ሰጠው፤ በእሥር ቤቱ አለቃ ልብ ውስጥም ይቅርታንና ርኅራሄን ጨመረለት፤ የእሥር ቤቱ አለቃም ዮሴፍን በእሥረኞቹ ላይ ሾመው እግዚአብሔር ከእሱ ጋር ነበርና ሥራውንም ሁሉ እግዚአብሔር ያቃናለት ነበር እንዳለ። (ዘፍ 39÷20) ዳዊትም በችግሩ ጊዜ ከእርሱ ጋር አለሁ እንዳለ። (መዝ 90÷15) ጌታችንም እኔ እስከዓለም ፍፃሜ በዘመኑ ሁሉ ከአንተ ጋር እኖራለሁ እንዳለ። (ማቴ 25÷20)

፰፯. እንደዚህም ሁሉ እግዚአብሔር ከከበረች እና ከተመረጠች ወለተ ጴጥሮስ ጋር ነበረ በነፍሰ ገዳይ አረማዊ ፊትም ሞገስን አገኘች። የወደደ ሁሉ ወደ አንች መጥቶ ይቀመጥ፤ እጅግ ቢበዙም አላዝንም፤ አልከለክላቸውምም፤ ከዚህ አስቀድሞ ግን ሰውን ባየ ጊዜ ሁለትም ቢሆኑ ሦስትም ቢሆኑ ሊገድላቸው ይከተላቸዋል፤ እግዚአብሔር ግን ከዐይኖቹ ይሰውራቸዋል። በፈለጋቸውም ጊዜ አያገኛቸውም፤ ነገር ግን ዛሬ የደግነቷን ሥራ ያደረባትን ግርማና ሞገስ ባዩ ጊዜ ከክፋት ወደ ቸርነት ተመለሰ። እንዲቀመጡም ፈቀደላቸው፤ ብዙ ስደተኞችም ከወዲያና ከወዲህ ወደ እሷ ተሰበሰቡ። ንቦች ወደ አውራቸው እንደ ሚሰበሰቡና እንደሚከቡት ከበቧት፤ ወንዶችና ሴቶችም በዙ ማኅበርም (ገዳም) መሠረቱ የመጀመሪያውም ማኅበር ይህ ነው።

፫፲፱. እየመራቻቸውም ቅድስትና የተመረጠች ወለተ ጴጥሮስ ሦስት ዓመት ተቀመጠች። ስመ ኃይለ ማርያም የተባለ እሥረኛ መነኩሴ በዚያ ነበረ፤ ስለቀናች ሃይማኖት በጽኑ እሥራት እግሩን የታሠረ ነው። ይኸውም ጻድቅ መነኩሴ ነበረ በዚያ ቦታም ማንም ሳያየው ከእሷ አስቀድሞ ነበረ፤ የተከበረችና የተመረጠች እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ባየችው ጊዜ ፈጽማ አዘነች ስትረዳው ስትመግበው ኖረች እንዲህም ሲል ትንቢት ተናገረላት "አንች ከዚህ ትወጫሽ እኔ ግን በዚህ እሞታለሁ ነገር ግን አንች ሳለሽ የሞትሁ እንደሆነ አንችም ገንዘሽ የቀበርሽኝ እንደሆነ በኋለኛው ዘመን በዓለም በሚመጣ ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚምረኝ ያ ካልሆነ ግን እንደማይምረኝ አውቃለሁ" አላት።

፪. ቅድስትና ብጽዕት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ሦስት ዓመት በዚያ ከተቀመጠች በኋላ ወንድሟ ዮሐንስ ወደ ንጉሡ ልጅ ወደ ፋሲለደስ ገብቶ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስን ከእሥር ቤት እንዲያወጣት እንዲነግረው ለመነው በአረማውያን ምድር ብትሞት መልካም ነውን ከዚህ በፊትም ታማ ነበር፤ ለሞትም ጥቂት ቀርቷት ነበር። እንደዚህስ አይሁን በእናንተና በእኛ መካከል የሚያሳዝን ነገር አይኑር አለው። እሱም ወደ ንጉሡ ገብቶ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ በዚያው እንዳትሞት ወንድሟ እንዳያዝኑብህ ከጋርበል እንዲያወጧት እዘዝ አለው እነሱ ይወዱሃልና ለመንግሥትህም ይቀናሉና ንጉሡም መለሰ እንደቃልህ የተናገርኸው ይደረግ አለው።

ያን ጊዜ ንጉሥ አገልጋዮቹን ወደዚያ ነፍሰ ገዳይ አረማዊ ልኮ ትጠብቃት ዘንድ ያዘዝሁህ ወለተ ጴጥሮስን ስደድልኝ አለው፤ መልእክተኛዉም ያርሶ የንጉሡን መልእክት ለዚያ ነፍሰ ገዳይ አረማዊ ነገረው ለእሷም ውጭ እንደ ተባለች ነገራት።

፮፩. ይህንንም በሰማ ጊዜ አስቀድመን ስሙን የጠራነው እሥረኛ ፈጽሞ አዘነ፤ ተስፋም ቆርጦ "ከእንግዲህስ እግዚአብሔር እንዳማይምረኝ አወቅሁ" አለ። ነገር ግን እግዚአብሔር ይቅር አለው፤ ማዳኑንም በላዩ ላይ አሳዬ፤ ታል ኪዳኑንም በአሐዛብ መካከል ገለጠ። ያን ጊዜ ያ እሥረኛ ታመመ፤ ቅድስትና ቡርክት እናታችንንም እንደዚህ አላት "እኔን ሳትቀብሪ እንዴት ትሔጃለሽ?" አላት፤ እሷም ሳልቀብርህ አልሄድም ባለችው ጊዜ ተደሰተ እጇን ሳማት፤ ከዚህ በኋላ ቅድስት እናታችን ይህን ነፍሰ ገዳይ አረማዊ ለመነችው "የንጉሥ ምልክት አልደረሰኝም አንተም ውሸትህን ነው ብለህ ምክንያት ፍጠር" አለችው፤ እሱም እሽ በጀ አላት፤ እንዳዘዘችውም አደረገ።

ያም መልእክተኛ ተመልሶ ሔዶ፡ ይህን ነገር ለንጉሥ ነገረው፡ ያን ጊዜ ንጉሥ ተቆጣ ሁለታችውም በሚያውቁት ምልክት ጻፈና ዳግመኛ ያን መልእክተኛ ላከው፤ ያም እሥረኛ በታመመ በሰባተኛው ቀን ዐረፈ፤ የተመኘውን አገኘ፤ በምስጋና በጸሎት ቀበሩት፤ ከሰንሰለቱም ጋር ወደ መቃብር አወረዱት፤ ሰንሰለቱ የማይፈታ ጽኑ ነበርና ገድሉን ፈጸመ በሰላምም ዐረፈ። ልመናውና በረከቱ ከእኛ ጋር ይሁን፤ ለዘለዓለሙ አሜን።

፮፪. ከዚህ በኋላ የንጉሥ መልእክተኛ ደርሶ የንጉሡን ደብዳቤ ለዚህ ነፍሰ ገዳይ አረማዊ ሰጠው፤ ተቀብሎም የንጉሡ ቃል መልካም ነው አለ።

ወዳጆቼ ሆይ! ለምድራዊ ንጉሥ ማንንም ይገድል ዘንድ ያለ ፈቃደ እግዚአብሔር ሥልጣን እንደሌለው አያችሁን በሥጋና በነፍስ ለነገሠ ለሰማያዊ ንጉሥ ግን ሁሉ ይቻለዋል፤ ይገድል ያድን ዘንድ ይቻለዋል።

፱፫. ንጉሥ ሱስንዮስ የተመረጠች የከበረች ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስን ይገድላት ዘንድ ብዙ ጊዜ ወደደ። በሠይፍ ሊቆርጣት የወደደበት ጊዜ ነበረ፣ ይኸውም በፊቱ በቆመች እና በዘለፈችው ጊዜ ነው። አማካሪዎቹም ወገኟ ዳዋሮ እና ፈጣጋር ሁሉ ጠላቶችህ ይሆናሉ ብለው አስተውት ዳግመኛ ሰይጣናዊ ጥበብን ተራቀቀ የእሱን ክፋት ይሰውር ዘንድ ወደ ጋርበል ሰደዳት። ያንንም አረማዊ ለማደሪያዋ የሚሆን ጎጆን በበረሃ ሳር መካከል ሥራላት፤ ነፋስም በነፈሰ ጊዜ ከታች ሁነህ እሳትን ስደድባት፣ ያቃጥላት እና ትሞት ዘንድ ይህንንም ያደረግህ እንደሆነ በታላቅ ክብር አከብርሃለሁ አለው።

፲፬. ያም አረማዊ ሰው ንጉሡ እንዳዘዘው አደረገ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስንም በሳር መካከል ባለ ጎጆ መካከል አስቀመጣት፤ ይህም ሳር እጅግ ታላቅ ነበረ። ከሩቅ ሆኖ እሳቱን ሰደደው እንደ ክረምት ነጎድጓድ እየጮኸ ወደ ጎጆው ደረሰ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስንም እንደ አጥር በወዲያና በወዲህ ከበባት። ያን ጊዜ የሠለስቱ ደቂቅን ጸሎት ጸለየች "እሳትና መቀት እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል ምስጉን ነው ለዘለዓለም የተመሰገነ ነውና" የሚለውን ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው ጸለየች። ምንም ምን አትፈራም፤ አትደነግጥም ነበር። ሞታ የክብርን አክሊል ትቀዳጅ ዘንድ ትቸኩል ነበር እንጂ። ያን ጊዜ ያ እሳት ጠፋ ዝናብም እንደ ወረደበት ሆነ፤ እግዚአብሔርም በእሳቷ ላይ ኃይሉን ገለጠ፤ ሠለስቱ ደቂቅን እንዳዳነ አዳናት፤ እሷ ግን በመዳኗ አልደሰተችም አዘነች እንጂ። ከሕይወት ሞትን ትወዳለችና ጴውሎስም ልለሌድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ። ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና እንዳለ (ፊል 1÷23) ውን እንድትጠብቅ ነው እንጂ።

፲፭. ንጉሡም ሊገድላት ባልቻለ ጊዜ ያወጣት ዘንድ አዘዘ፣ ከዚህ በኋላ ያ አረማዊ ነፍሰ ገዳይ ንጉሥ እንዳዘዘ ውጭ እና ሊጅ አላት የተድላ

የደስታ ሁሉ አምላክ የምሕረት አባት በሆነው በአባቷ በእግዚአብሔር እየተደሰተች ወጥታ ሐዲች። ትሩፋን በባቢሎን እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ እጅግ ደስተኞች ሆንን ያን ጊዜ አፋችን ደስታን አንደበታችንም ሐሴትን ሞላ እንዳለ። (መዝ 125÷1)

ከሷ ጋር ያሉ እኅተ ክርስቶስ፣ ኢላርያ አርድዕቶቿም ተክለ ማርያምና አፅቀ ሐዋርያት እና ሌሎችም ደስተኞች መነኮሳትና መነኮሳዊያት ከሷ ጋር አብረው ወጡ። ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ስትሔድ ከደምቢያ አውራጃ ጫንቆ ደረሰች፤ ጥቂት ጊዜም ተቀመጠች ልትኖር ወደ ወደደችው አገር አድርሷታልና።

፶፮. በየአገሩ ሁሉ የተበታተኑ፣ ቆባቸውን አስወግደው ሰብዓ ዓለምን መስለው የሚኖሩ ወንዶችም ሴቶችም መነኮሳት ወደ እርሷ ተሰበሰቡ፤ ልጆችም ሆኗት። መጽሐፍ ስለአባቶሽ ፈንታ ልጆች ተወለዱልሽ በምድር ሁሉ አለቆች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ ስምሽንም ለልጅ ልጅ ያሳስቡልሻል እንዳለ (መዝ 44፥16) በየቀኑ ይበዛሉ፤ አንድ ማኅበርም ሆኑ ይኸውም ሁለተኛ ማኅበር ነው።

፶፯. ቡርክት ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ እያለች ጽኑዕ ደዌ ተነሣ ከነሱ ወገን ብዙዎች ታመሙ ስለዚህ የሃገሩ ሰዎች ፈሩ አንሳራሳር እኒህ መጻተኞች ከባድ በሽታ አመጡብን አሉ ከነሳቸው ራቁ ወደነእርሱ ከመቅረብ ተከለከሉ። ከዚህ በኋላ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ በዚህ ብንኖር የሞተውን የሚቀብርልን አናገኝም ጅብም ይነጣጥቀናል ወደ ደሴተ አንገራ ብንገባ ይሻለናል አለች። ካሉበት አገር ደሴቲቱ ቅርብ ናት ፈጥነው ተነሥተው ድውዮቻቸውን ተሸክመው ወደዚያ ደሴት ገቡ። በዚያም ተቀመጡ።

የለባሲተ ክርስቶስ ልጅ የምትሠን መልከ መልካም ድንግል ብላቴና በዚያ ነበረች፤ ፈጽማ እየተጋች ለሁሉ ታገለግል ነበር:: በትልቁም በትንሹም ላይ አታንገራግርም ያለ አድልዎ ለሁሉም ታገለግል ነበር እንጂ:: ከዕለታት በአንድ ቀን በዕለተ ሐሙስ የሚጸለይ የእመቤታችን ምስጋና ስትጸልይ ሳለች እኅተ ክርስቶስ ጠርታ አዘዘቻት፤ እሷም ወደ ታዘዘችበት ቦታ ሔደችና ሥራዋን ጨርሳ ተመለሰች፤ ጸሎቷ በአንደበቷ ላይ ነበር ገና አልጨረሰችውም ነበር:: ዳግመኛ ጠራቻትና ሁለተኛ አዘዘቻት ዳግመኛ ምስጋናው በአፏ ላይ እያለ የተላከችውን ለመፈጸም ሔደች:: ከዚህ በኋላ እመቤታችን ወደ እርሷ መጥታ "ስለምን ታደክምሻለች የያዝሽውን ጸሎት ቶሎ ጨር፤ሺ ከዚህ ውጣ ውረድ እኔ አሳርፍሻለሁ ወደ ዘለዓለም ዕረፍት አገባሻለሁ" አለቻት:: ጸሎቷንም ከጨረሰች በኋላ እንደ ድካም ያለ ጥቂት ሕመምን ታመመች እመቤታችንም የነገረቻትን ነገረቻቸው ከነዚያ ከታመሙ ሰዎች ጋርም ዐረፈች::

፮፰. ያን ጊዜ ከአባ ዝክረ ማርያም በቀር መቃብር የሚቆፍር አልነበረም ያን ጊዜ የተከበረች የተመረጠች እናታችን ቅድስት ወለተ ጼጥሮስ እጅግ አዘነች፤ በትሕትና ቃልም እንዲህ አለችው:: "ወንድሜ ሆይ! እንዴት እናደርጋለን መቃብሩንስ ማን ይቆፍርልናል" አለችው:: እሱም በቁጣ ቃል መለሰላት "ከኔ ምን ትፈልጊያለሽ እኔንስ ምን ትይኛለሽ፤ እኔ እንደምቆፍር ታስቢያለሽን እኔ አላወቅም አልችልም:: ይልቁንም አንቺ ተነሽ ታጠቂና ቆፍሪ ሰዉን ሁሉ የሰበሰብሽና ይህንም ደቄ ያመጣሽ አንቺ አይደለሽምን አሁንስ ባንች ድካም ማን ይገባል አንች እንደጀመርሽ ጨርሽ እንጂ" አላት::

ዳግመኛ በትሕትና ቃል ለመነችው ያን ጊዜ ተቆጥቶ እያንጎራጎረ ተነሣ:: ቅድስት እናታችን ወለተ ጼጥሮስ የሚቆፍርበትን ቦታ አሳየችው:: መቆፈሪያውንም ይዞ ምድሪቱን አንድ ጊዜ ቢመታት ያን ጊዜ የመቃብር በር ተከፈተ ብዙ ሰው መያዝ የሚችል ከሆነ ጥልቅ

ጉድንድም ሆነ። ከዚያ አስቀድሞ ያን ቦታ የሚያውቀው አልነበረም፤ በቅድስት አናታችን ወለተ ጸጥሮስ ጸሎት ተገለጠ እንጂ። ያን ጊዜ እነዚያ ያረፉትን ደናግል ሥጋቸውን በዚያ አስቀመጡት ከነሱም በኋላ ብዙ እጉዶች አረፉ በዚያ ሥፍራም ተቀበሩ መንግሥተ ሰማያትንም ወረሱ፤ ልመናቸው በረከታቸው ይደረግልን። ለዘለዓለሙ አሜን።

ቅድስት አእናታችን ወለተ ጴጥሮስ በዚያ ሳለች ወንድሟ ዘድንግል ወደ እሷ ላከ። ከእንፍራዝ አጠገብ ባለችው ቦታየም ተቀመጭ፤ ለምለም ምድር ናትና እንጨትና ውኃም አላት። በዚያም መኖር ይሻልሻል አላት፤ ሰምታም የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን አለች።

፶፱. ከዚህ በኋላ ከገዳማትና ደሴቶችም ቦታዎችን መረመረች ዳጋም ቢሆን ጣናም ቢሆን ለመኖር የሚስማማትን መረመረች። ያን ጊዜ በታቦታቱ ላይ መስቀል አድርጋ ሦስት ሱባኤ በታላቅ ቀኖና እግዚአብሔር የምትኖርበትን ቦታ ያሳያት ዘንድ ጸለየች። ዕጣውም በሦስቱ ሱባኤ ሁሉ ወደ ደራ ምድር ወጣ ከዚህ በኋላ ንጉሥ ከደሴቶች በየትኛው እንድኖር ይፈልጋል፤ ብላ ወደ መልአከ ክርስቶስ ላከች። ሰዎችም ስለ ሃይማኖትና ስለቍርባንም እንዳይጣሉኝ ያዝዝልኝ አለችው። መልክአ ክርስቶስም ወደ ንጉሥ ገብቶ የሆነውን ሁሉ ነገረው። "በጣና ደሴት ውስጥ ትቀመጥ ዘንድ ፈቀድሁላት ማንም አይተናኮላት" አለው። ከዚህ በኋላ ከዚያች ደሴት ወጣች ተጉዛም ወደ ጣና ደሴት ደረሰች። በአንድ መነኩሴ በዓትም ገባችና በዚያ ተቀመጠች።

፫. ያን ጊዜ የጣናን መቅደስ አየችው፤ በፈረንጅ ዘመን ሴት ትገባ ነበርና ዳግመኛ የእመቤታችንን ሥዕል አሳዩአት ይህችውም በወርቅ ቀለም የተሳለች የግብፃውያን ሥዕል ናት። እጅግ ቀይ እጅግ ጥቁር አይደለችምና እንደ ኢትዮጵያ ሰዎች መልክ መካከለኛ ናት እንጂ። ያን ጊዜ የተመረጠችና የከበረች እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ “ይህች ሥዕል በእውነት እመቤታችንን ትመስላለች ከእሷ ጋርም ያሉት እመቤታችንን መቼ አየሻት” አሏት።

ያን ጊዜ ቃሏን ለውጣ ሰወረቻቸው፣ “አላየኋትም ይህች ሥዕል እመቤታንን ትመስላለች አልሁ እንጂ አየኋት አላልሁም” አለቻቸው። ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ በዚያ ቦታ ሦስት ጸሞችን ጸመች። እሊህም ጸመ ቁስቋም፣ የጌና ጸምና ተመረጠች ዐርብ ናት። ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ጣናን እንደ ከተማ ቁጠረችው ስለሰው ብዛት ነው። በዚያ መኖርንም አልወደደችም፤ በጽሙና የምትኖርበትን ቦታ ያሳያት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ጸለየች። የእግዚአብሔር መላክ ተገልጦ “ወደ ምጽሌ ሒጅ እሷ ክፍልሽ ናትና” አላት። የተመረጠችና የከበረች እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስም ወደ መልክአ ክርስቶስ ምጽሌ ገብቼ እንድኖር ይፈቀድልኝ ዘንድ ንጉሥን ለምንልኝ ብላ መልእክት ላከች፤ እሷ የጽሙና ቦታ ናትና በእሷ መኖርም ይሻለኛል አለችው። መልክአ ክርስቶስም እንዲሁ ለንጉሡ ካገረው ንጉሡም ፈቅጀላታለሁ ትኑር አለው።

ከዚህ በኋላ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ሐዳም ጽሌ ገባች። ይህችንም ደሴት ባየቻት ጊዜ ወደደቻት የመትቀመጥበትንም ቤት መረጠላት ባለቤቱ ጥሎት የተሰደደ ቤትም አገኙላት እሷም ገብታ ተቀመጠች።

፫፩. ከዚህ በኋላ የደብሩ መምህር ወደ እሷ መጣ ከሱም ጋር በፈረንጅ ሃይማኖት የሚያምኑ ብዙ መነኮሳት ነበሩ። "ንጉሡን የካድሽው ስትሆኚ ወደ ደብራችን ማን አገባሽ? ንጉሥ በእኛ ላይ ይቆጣል ይበቀልንማል በሰላ ከእኛ ዘንድ ሒጅልን ያ ሳይሆን ግን እኛ ካንቺ ጋር እንጣላለን" አሏት። ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስም በትሕትና ቃል መለሰችላቸው "ንጉሥ በፈለግሽው ቦታ ኑሪ ያለኝ አይደለምን! ከጠላችሁኝ ከእናንተ ዘንድ እሔዳለሁ ደብራችሁንም እተውላችኋለሁ ከዚህም ብቀመጥ የሚነካችሁ ምንም የለም" አለቻቸው። ያን ጊዜ ተዋትና ሔዱ፤ በትሕትና ቃል አሸንፋቸዋለችና። ጳውሎስ ክፉን በክፉ አትቃወመው በጎ ሥራ በመሥራት አሸንፈው እንጂ (ሮሜ 12፡ 21) እንዳለ። ሐዋርያ ጴጥሮስም እግዚአብሔርን የማያውቁ ሰነፎችን በመልካም ስራችሁ አፋቸውን ታዝዘንቸው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይህ ነውና ብሏል።

፫፪. ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ በእርጋታና በጸጥታ ኖረች፤ ብዙ ሰዎች ሴቶችም ወንዶችም ወደ እሷ ተሰብስበው ከሷ ጋር ኖሩ። የአምባ ማርያም ጸጋ ክርስቶስም ከዚያ ነበረ። አንድ ማኅበርም ሆነ ይኸውም ሦስተኛ ማኅበር ነው። በዚያ ወራት በካቶሊክ ሃይማኖት ሳለ የሞተው ሥዕለ ክርስቶስ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ምጽሌ ከብዙ ሰዎች እንዳለችና ቍርባንንም እንዳልተቀበለች ሰማ። እጅግ ተበሳጭቶ ደነፋ፤ "በውኑ ሴት ታሸንፈኛለችን? ወደ እሷ ሒጄ በጅራፍ እገርፋታለሁ፣ ጕንጯንም እጸፋታለሁ፣ በካቶሊክ ሃይማኖት እንድታምን ቍርባኑንም እንድትቀበል አደርጋለሁ" አለ።

፫፫. እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስም በሰማች ጊዜ በሌሊት ከምጽሌ ወጥታ ሸሸች ዛሬ ወዳለንበት ቆራጣ ገዳም ደርሳ ተሸሸገች። ከዚያም ወደ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሒዳ በዕቃ ቤቱ ተሸሸገች፤ ጥቂት ጊዜም በዚያ ተቀመጠች። ሥዕለ ክርስቶስም በታንኳ አልፎ ሒደ በእሷ ላይ ክፉ ነገር ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር አልፈቀደለትምና

የመከራትም ምክርም ብላሽ ሆነች የመዘመር መጽሐፍ የአለቆችን ምክራቸውን ያስረሳቸዋል (መዝ 32፡11) ይላልና። ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ በሞትና በግርፋት ፍርሃት የሸሸች አይደለም አምላክህ እግዚአብሔርን አትፈታተነኸው የሚል ጽሑፍ ስላለ ነው እንጂ። (ዘዳ 6፡16፣ ማቴ 4፡7)

ከዚህ በኋላ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ተመልሳ ምጽሌ ገባች ዳግመኛ መዝራዕተ ክርስቶስ በደራ አውራጃ ያሉ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት ያልገቡትን ክርስቲያኖች ያሥር ዘንድ ከንጉሡ የፈቃድ ደብዳቤ ተቀብሎ እንደመጣ ሰማች። "አንቺንም ይፈልግሻል እነሆ ደረሰ" አሏት። ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ሰምታ ዳግመኛ ወጣች፣ ወደ ሰደጭላ ሸሸች፣ ሰላምም ሆነ ዳግመኛ ወደ ምጽሌ ተመለሰች።

ፀ፬. ዳግመኛ በመርከብ ለብቻዋ አድርጋችሁ ያለቀዛፊ ስደዷት፤ ነፋስ ሲነፍስ፣ ማዕበሉም ያሰጥማትና ትሞት ዘንድ አሉ። ያን ጊዜ ታንኳ ከባሕሩ በላይ ከፍ ከፍ አለ፤ ፍላጻ እንደሚበር በራሪ በረረ ሔዶም ወደ ወደቡ አደረሳት፤ ዳግመኛም ተመልሶ ወደ ቀድሞው ቦታ አደረሳት። ለዚህም ታምራት ብዙ እጎቶችና ወንድሞች ምስክር ሆኑ ቃላቸውም አንድ ሆነ።

ከዚህ በኋላ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ ምጽሌ ገብታ በሰላም ተቀመጠች። ከእሷ ጋርም ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ቁጥራቸውም ሃምሳ ያክል ነበር። በአንድ ቤትም ይቀመጣሉ፤ በአንድነትም ማዕዳቸውን ይባርካሉ፤ በተድላና በደስታም ይመገባሉ፤ በመኝታ ጊዜ ነው እንጂ። ወንዶችም ሴቶችም በምንም በምንም አይለዩም ነበር። ኃጢአትን ማሰብ በልባቸው አልነበረምና፣ ሁሉም ንጹሐን ናቸውና፣ የዝሙትን የስስትን መናፍስት በቤቱ ውስጥ ሥልጣን የላቸውም ብላ እሷ እንደመሰከረች። ከእነሱ አንዱ ስሙ መርቆሬዎስ የሚባለው በክንፉ እየበረረ ወደ ዘጌ ይሔድ ነበር።

፻፭. የተመረጠችና የተከበረች ቅድስተት ወለተ ጴጥሮስ በዚያ ሳለች ስሙ መልክአ ክርስቶስ ወረኛ ሹም ተነሣ። ራሱንም በላስታ ሾመ፤ ከእሱ የተላከ ቢሆኖ የሚባል ሰው ከሠራዊቱ ጋር መጣና ንጉሡንም ከበበና መንግሥቱንም ሊቀማ ወደደ። ያን ጊዜ ፈራ ደነገጠ ለእግዚአብሔር ኃይልና ብርታትን ቢሰጠኝ ይህንን ከሀዲ በእጄ ቢያስገባው በዲዮስቆሮስ ሃይማኖትም አምናለሁ፤ የተናቀች የልዮንን ሃይማኖት አጠፋለሁ ብሎ ተሳለ። እንዳለውም ሆነለት፤ አሸንፎ ገደለው፣ በሰላምም ተመለሰ።

ከዚህ በኋላ ዐዋጅ አስነገረ "በካቶሊክ ሃይማኖት የሚያምን ቃሌን ከሰማ በኋላትእዛዜንም የተላለፈ ቢኖር ቤቱ ይዘረፍ፣ ሞትም ይፈረድበታል። የተሰደዱ ክርስቲያኖችን ሁሉ በየአገራቸው በየርስታቸው ይመለሱ" አለ። ለክርስቲያኖችም ታላቅ ደስታ ሆነላቸው፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ከዚህ በኋላ ንጉሡ የደስታ ደብዳቤ ወደ እናታችን ቅድት ወለተ ጴጥሮስ ላከ። እንዲህም አለ፦ "የካቶሊክን ሃይማኖት አጥፍቼ የክርስቲያንን ሃይማኖት መልሻለሁ ደስ ይበልሽ ደስታም ይገባሻል። ከእንግዲህስ ወዲህ በአንቺና በእኔ መካከል ሰላም ይሁን" አላት። የንጉሡም መልእክተኛ ወደ ተመረጠችና ወደ ከበረች እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ደርሶ እንዲህ የምትለውን ደብዳቤ ሰጣት። ተቀብላ አነበበችና በታላቅ ቃል እልል አለች። በመጽሐፈ መዝሙር አሕዛብ ሁላችሁ በእጆቻችሁ አጨብጭቡ በደስታ ቃልም ለእግዚአብሔር እልል በሉ እንደ ተባለ (መዝ 46፣1) ከእሷ ጋር ያሉ ካህናትም ምስጉን የተመሰገነ እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን እያሉ አመሰገኑ። ይህም የሆነው ሐምሌ ሦስት ቀን ነበረ።

፻፮. በነጋውም የንጉሡ መልእክተኛ ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስን "ንጉሥ ይህን የምሥራች አደርስ ዘንድ ወደ ጣና ልኮኛልና እንድሔድ ፍቀጅልኝ" አላት። ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስም "አባ ዘሥላሴን ይህን በብላቴና ወደ ጣና አድርሰው፤ በዚያም ለጴጥሮስ ወጳውሎስ

በዓል የሚሆንን ዓሣ አጥምድልኝ" አለችው። እሱም እሽ አላት በረከትንም አሳደረችበት እና ሸኘችው። ከንጉሡ መልእክተኛ ጋር ሔዶ ጣናም አደረሰው ያን ጊዜ መረቡን ወደ ባሕር ላይ ጣለ ዓሳም ተያዘለት። ዓሣ ሲያጠምድ ውሎ ወደ ምጽሌ ተመለሰ።

ዐሥራ ሦስት ዓሣ ይዞ ገባና በእናታን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ ፊት አቀረበ። "በአንቺ በረከት እግዚአብሔር የሰጠኝን እነሆ አምጥቻለሁ" አላት። እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስም እነዚህ ዐሥራ ሁለቱ ዓሳዎች እንደ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ እንደ መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የሐዋርያት በረከት የመምህራቸውም የክርስቶስ በረከት ይደርባችሁ፤ እሱም አሜን ይሁን ይደረግልኝ አላት። በእውነት ይህ ነገር ቍጥሩ ሳይጎድልም ሳይቀንስም የሆነ ይህ ነገር ድንቅ ነው። በነጋውም የጴጥሮስ የጳውሎስ በዓል ተደረገ። ያንንም ዓሣ ወጥ አደረገችው፤ የማኅበረ መነኰሳቱን የደብሩንም አገልጋዮች ጋበዘች።

፱፯. ይህ በሐምሌ ወር ከተደረገ በኋላ በመስከረም ዐሥር የጼዴንያ በዓል ዕለት ንጉሥ ሱስንዮስ ሞተ፤ በእሱ ፈንታ ልጁ ፋሲለደስ ነገሠ፤ ሃይማኖትንም አቀና። በዚያ ወራት በቱሪ አገር ታሥሮ የነበረው የምጽሌው መምህር አባ አጽፈ ክርስቶስና ሌሎችም በካቶሊክ ሃይማኖት የተሰደዱ መነኰሳት ተመለሱ። ከዚህ በኋላ እናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ አንድ ዓመት ተቀመጠች ለቅዱስ ፋሲለደስ የክርስቲያን ሃይማኖት ብትመለስ አንድ አመት እቀመጣለሁ ዘመቅያስህም ቍርባንን እቀበላለሁ ብላ ተስላ ነበርና። በተሰደዱ ካህናት እጅ ቍርባንን ስትቀበል ኖረች። ካህኑ ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ሲል የመንፈስ ቅዱስን መውረድ በግልጽ ታይ ነበር።

፫፲. ምሽት በሆነ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ገብታ በእመቤታችን ሥዕል ፊት እንደ ተተከለ ምሰሶ ሆና ትቆማለች። ወደ ግድግዳም ወደ ምስሶም አትጠጋም፤ ስለ ሕገዘቡና ስለ ራሷ ትጸልያለች፣ ትማልዳለች። ያለፅረፍት ሌሊቱን በሙሉ ስትጸልይ ታድራለች። ማለዳ ፀሐይ ሲወጣ ስንክሳር ተነቦ የሰርክ የስንበት ጸሎት በተደረገ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ትወጣለች፤ ወደ ቤቷም ትገባለች፤ የዮሐንስ ወንጌል ታነባለች፤ ሁል ጊዜም እንዲህ ታደርጋለች።፤ እንደ አባ አርሳንዮስ ሆነች።

በደቄ ምክንያት ከዓለም የወጣች አንዲት ሴት በዚያ ነበረች ዕድሜዋም ሠላሳ ዘጠኝ ነበረ፤ ደም እየፈሰሳት ብዙ ጊዜ ትፈተን ነበር። ብዙ ጊዜም ትታመማለች ለጸሎት በቆመች ጊዜ ወደ እመቤታችን ሥዕል ትለምንላታለች "እመቤቴ ሆይ በአማላጅነትሽ ይህ ደም ይደርቅልኝ ዘንድ እለምንሻለሁ እጅግ ተቸግራለችና" አለቻት። ያችም ሥዕል አነጋገረቻት "ዘወትር አትዘባገዚኝ እነሆ ልመናሽን ሰምቻለሁ መከራዋንም አይቻለሁ ደሟንም አድርቄአለሁ ከእንግዲህ ወዲህ ደም ፈጽሞ አይታይባትም" አላት፤ ያን ጊዜ ደሟ ቆመላት። ደም ለመቁረጥም እድሜዋ ገና አልደረሰም ነበርና።

፳፬. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሃይማኖትሽ አድኖሻል እንዳላትና የልብሱን ጫፍ እንደዳሰችው ሴት ሆነች ከሕመምዋም ተፈወሰች። በእናታችን ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ የፈወሳትን ፈጣሪዋን ለማመስገን በሃይማኖት ከእመቤታችን ሥዕል ፊት ቆመች። እነዚህም ስደተኞች ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስን ሲጎበኙ ኖሩ። በስደት ጊዜ ያገኛቸቸዉን መከራ እያንዳንዱን ከእርሷ ጋር ይጨዋወታሉ፤ ዳግመኛም በመመለሳቸው ይደሰታሉ፤ እርስ በርሳቸዉም እንዲህ ይባባላሉ። ጳውሎስ እንደተናገረ ተስፋ የምናደርጋት ሕይወታችን

ቀረበች ሌሊቱ አልፎ አልፎ ቀኑ ቀረበ ይላሉ። (ሮሜ 13፣11) ዳግመኛም በፈረንጆች ወጥመድ ያልጣለን፤ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ነፍሳችን እንደወፍ ከአዳኝ ወጥመድ አመለጠች ወጥመዱ ተሰበረ እኛም አመለጥን ይባባላሉ። (መዝ 123፣6)

ኛኒ. በዚያ ወራት ቅድስት እናታችን ወለተ ጴጥሮስ የአባ ዮሐንስ መታሰቢያ አደረገች። እሱ በተሰደደበት በአምባ ማርያም አርፏልና ለዚያ ደብር አገልጋዮች እና ለማኅበሩ ሁሉ ብዙ መብልና መጠጥ አቀረበች። ያላትን ሁሉ ጨረሰች ለነገም አላተረፈችም። ቅዱስ ወንጌል ለነገ አትበሉ ነገ ለራሷ ታስባለችና እንዳለ። (ማቴ 6÷33)

ከመነኮሳት አንዱ አይቶ አንጎራጎረ፣ "ያለአቅም የዕለት እንጀራ ሲይኖረን ይህን ሁሉ መስጠት ምንድን ነው? ይህ ሁሉ ስለ ውዳሴ ከንቱ አይደለምን ነገ የምንበላው የለንም" አለ። እኅተ ክርስቶስም ተቈጣችው፤ "ከዕውቀት የደኸየህ ተስፋ የሌለህ እግዚአብሔርን ድሃ አደረግከውን ለጠራው ሁሉ የሚበቃ ባለጸጋ አይደለምን ዛሬም እሱ ነው ነገም እሱ ነው።" ያን ጊዜ ያላሰቡትን እና ከዚህ ቀድሞ የማያውቁትን ጫን እህል ከወዲያ አራት ጫን እህል ከወዲህ ይዘው መልእክተኞች መጡ። ይህን ባዩ ጊዜ አደነቁ እግዚአብሔርንም አመሰገኑት።